የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፶፰
አዲስ አበባ ሰኔ ፳፯ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

26th Year No.58
ADDIS ABABA 4th July, 2020

ማውጫ

Content

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፯/፪ሺ፲፪ ዓ.ም

የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤትን ህጋዊ ሰውነት ለመስጠት የወጣ አዋጅ…ገጽ ፲፪ሺ፮፻፲፫

Proclamation No.1207/2020

A proclamation to provide Legal personality to Ethiopian Islamic Affairs General Council ……………………….…….…..................Page 12,613

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፯/፪ሺ፲፪

የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤትን ህጋዊ ሰውነት ለመስጠት የወጣ አዋጅ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት አንቀጽ ፳፯(፪) በዜጎች የሃይማኖት አስተዳደር ተቋማት የማቋቋም መብት በመጠቀም ኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞች ያቋቋሙትን ሀገር አቀፍ ተቋም የህግ ሰውነት በህግ መስጠት በማስፈለጉ፣

የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት በተግባር ደረጃ እውቅና ያለው የህዝብ ተቋም እንደመሆኑና ከፍተኛ የህዝብ ቁጥር ያለውን የሙስሊም ማህበረሰብ በመንግስት ዘንድና በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚወክል በመሆኑ ህጋዊ ሰውነትና እውቅና በአዋጅ መስጠት አስፈላጊ በመሆኑ ፡

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት አንቀጽ ፶፭(፩) መሰረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

PROCLAMATION No.1207/2020

A PROCLAMATION TO PROVIDE LEGAL PERSONALITY FOR ETHIOPIAN ISLAMIC AFFAIRS GENERAL COUNCIL

WHEREAS, it has become necessary to provide legal personality on the national institution organized by Ethiopian Muslims in accordance with the right to establish citizens' rights to religious administration institutions based on Article 27(2) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia.

WHEREAS, it has become necessary to provide legal personality to Ethiopian Islamic Affairs General Council which is a public institution that has a defacto recognition and that represents a large number of Muslim community in relation to the government as well as internationally.

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

ያንዱ ዋጋ
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤትን ህጋዊ ሰውነት ለመስጠት የወጣ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፯/፪ሺ፲፪" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

፪. ህጋዊ ሰውነት

የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤትና በስሩ የተቋቋሙና የሚቋቋሙ የሃይማኖት ተቋማት ድርጅቶችና ማህበራት የተለየ ምዝገባ ሳያስፈልጋቸው በዚህ አዋጅ መሰረት የህግ ሰውነት ተሰጥቷቸዋል፡፡

፫. ስያሜ

ተቋሙ በሙሉ ስሙ "የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት" ተብሎ የሚጠራ ሲሆን ለአርማ ፣ ለማህተምና ለቲተሮች አጠቃቀም አመቺነት እንደአስፈላጊነቱ በአጭር ስም ሊጠራ ይችላል፡፡

፬. ስለበጀት

፩/ የምክር ቤቱ በጀት ከሀገር ውስጥና ከውጪ ሀገር በሚገኙ ስጦታዎች፣ ከሙስሊሙ ማህበረሰብ በሚሰበሰቡ መዋጮዎች፣በሃይማኖቱ ከተፈቀዱ የአገልግሎት ክፍያዎችና እርዳታዎች የሚሸፈን ይሆናል፡፡

፪/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ሌሎች በሀገሪቱ ተፈፃሚነት ያላቸውን የታክስና የንግድ አሰተዳደር ህጎች መሠረት አድርጎ ተጨማሪ የገቢ ማስገኛ እና የልማት ሥራዎችን ይሰራል

፫/ ምክር ቤቱ ግልፅ የፋይናንስና የገንዘብ አስተዳደር ሥርዓት ይኖረዋል፡፡

፭. የስራ ቋንቋ

የምክር ቤቱ የስራ ቋንቋ የፌደራልና የየክልሉ የሥራ ቋንቋዎችን መሰረት አድርጎ በመተዳደሪያ ደንቡ ይወሰናል፡፡

1. Short Title

This Proclamation may be cited as "A proclamation to provide Legal personality to Ethiopian Islamic Affairs General Council No. 1207/2020".

2. Legal Personality

In accordance with this Proclamation Ethiopian Islamic Affairs General Council and religious institutions, organizations and societies established and to be established under it shall have legal personality without requirements of especial registration.

3. Heading

The institution may be cited with its full name "Ethiopian Islamic Affairs General Council" and may also be referred to using an abbreviation for convenience of usage in emblems or official seal or stamps as may be necessary.

4. Budget

1/ The budget of the Council shall be covered by gifts obtained from in and out of the country, Contributions collected from Muslim communities, service fees and donations allowed by the religion.

2/ Without prejudice to the provision of Sub-Article (1) of this Article the Council can engage in additional income generating and development activities pursuant to other tax and commercial administration laws of the country.

3/ The Council shall establish a clear and transparent Financial Administration system.

5. Working Language

The working language of the Council shall be determined by bylaws taking in to account the Federal and Regional working languages.

፮. <u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች</u>

፩/ ከዚህ አዋጅ በፊት በሁሉም የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት (መጅሊስ) ተብለው በሚጠሩ የምክር ቤቱ አካላት ያፈሯቸው ንብረቶች፡ መብትና ግዴታዎቻቸው በሙሉ እንደተጠበቁ ይቆያሉ፡፡

፪/ ጠቅላይ ምክር ቤቱ የውሰጥ አሰራሩን እና አደረጃጀቱን ለመወሰን ደንብ ያወጣል፡፡

፫/ የዚህ ምክር ቤት መቋቋም የሀገሪቷ ሙስሊሞች በክልልም ሆነ በፌዴራል ደረጃ የመሰረቷቸውን በሃይማኖት የተደራጁ ተቋማት መብትም ሆነ ለወደፊቱ የመደራጀትና የመመዝገብ መብታቸውን አይከለክልም፡፡

፯. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ዕለት ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ሰኔ ፳፯ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም

ሳህለወርቅ ዘውዴ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ
ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

6. <u>Transitory Provisions</u>

1/ All properties, obligations and rights obtained before the effective date of this proclamation by all organs of the Ethiopian Islamic Affairs General Council (Mejlis) remain valid.

2/ The General Council may issue Regulation for its internal activity and organization

3/ This Proclamation shall not affect the rights of other religious institutions established by Ethiopian Muslims either at the Federal or Regional level or their right to organize and be registered in the future.

7. <u>Effective Date</u>

This Proclamation shall enter into force on the date of publication in the *Federal Negarit Gazette.*

Done at Addis Ababa, on this 4th day of July, 2020.

SAHELWORK ZEWDE

PRESIDENT OF THE FEDERAL
DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት የዘካ ኮሚሽን ማቋቋሚያ ደንብ

ደንብ ቁጥር 3/2018

THE ETHIOPIAN ISLAMIC AFFAIRS SUPREME COUNCIL

ሕዳር 2018/ጁማደል ኡላ 1447

بسـم الله الرحمن الرحيم

የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት የዘካ ኮሚሽን ማቋቋሚያ ደንብ

መግቢያ

የሀገራችን ሙስሊም ማህበረሰብ ከአምስቱ የእስልምና ሀይማኖት ማእዘናት አንዱ የሆነውን የዘካ ግዴታውን በአግባቡ ለመወጣት የሚያስችለው አሰራር ስርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

ዘካ ለማህበረሰቡ እንዲያያሳካ በእስልምና ሀይማኖት ውስጥ የተቀመጡትን ዓላማዎች ከግብ ለማድረስና ዘካ ለድህነት ቅነሳ እና ለሀገር ልማት ያለውን አቅም ተግባራዊነት በሚያረጋግጥ መልኩ የሚተዳደርበት ተቋም በሀገራችን ባለመኖሩ፣

የዘካ አሰባሰብ እና አከፋፈል ግልጽነት፣ ተጠያቂነትና ተዓማኒነት ባለው ተቋምና አሰራሩም ሸሪዓውና የሀገራችንን ተፈጻሚነት ያላቸውን ህጎች እንዲሁም ወቅቱ የደረሰበት የኢኮኖሚ ስርዓትና ቴክኖሎጂን ባዋጀ መልኩ ማስኬድ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የዘካ ሰጪዎች እና የዘካ ተቀባዮችን ፍላጎት መሠረት ያደረገ በማህበረሰቡ ታአማኒነት ያለው፣ ህጋዊ ሰውነት ያለው፣ ዘመናዊ አሰራር እና አደረጃጀት የሚከተል በነፃነት ሥራዎቹን የሚሰራ ኮሚሽን ማቋቋም ከምንጊዜውም በላይ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፤

በመሆኑም በኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤትን ሕጋዊ ሰውነት ለመስጠት በወጣው አዋጅ ቁጥር 1207/2012 አንቀጽ 6(2) ጠቅላይ ምክር ቤቱ አሰራሩን እና አደረጃጀቱን ለመወሰን በተሰጠው ደንብ የማውጣት ስልጣን መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷዋል::

አንቀጽ 1
ርዕስ

ይህ ደንብ "የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት የዘካ ኮሚሽን ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 4/2018" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

አንቀጽ 2
ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም ካላሰጠው በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ የሚከተለው ትርጉም ይኖራቸዋል:-

THE ETHIOPIAN ISLAMIC AFFAIRS SUPREME COUNCIL

1. “ዘካ” ማለት ማንኛውም ሙስሊም በህጋዊ መንገድ ካፈራው ከሚንቀሳቀስና ከማይንቀሳቀስ ሀብትና ንብረቱ ላይ በሃይማኖቱ በተደነገገው መጠን፣ ሥርዓትና ጊዜ ለሚገባቸው ወገኖች እንዲሰጥ የሚያወጣው የአምልኮ አካል የሆነ የግዴታ መዋጮ ነው፡፡
2. “ኮሚሽን” ወይም “ኮሚሽኑ” ማለት በዚህ ደንብ መሰረት የተቋቋመው የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት የዘካ ኮሚሽን ማለት ነው፡፡
3. “ባለአደራ ቦርድ” “ቦርዱ” ማለት የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት የዘካ ኮሚሽን ባለአደራ ቦርድ ማለት ነው፡፡
4. **“ፈትዋ”** ማለት በህብረተሰቡ ውስጥ ለሚነሱ ሃይማኖታዊ ጉዳዮች ላይ በኃይማኖቱ ሊቃውንት (ኡለሞች)፣ በሸሪዓ ተስማሚነት አማካሪዎች ወይም በኡለሞች ምክር ቤት የተላለፈ መሰረታዊ የኃይማኖት ምንጮች እና የእስልምና አስተምህሮቶችን መሠረት ያደረገ አስገዳጅ ውሳኔ ነው፡፡

<u>አንቀጽ-3</u>
<u>የዘካ ኮሚሽን መቋቋም</u>

1. የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት የዘካ ኮሚሽን እራሱን የቻለ ሕጋዊ ሰውነት ያለው የሀይማኖት አስተዳደር ተቋም ሆኖ በዚህ ደንብ መሰረት ተቋቁሟል፡፡
2. ኮሚሽኑ በሙያና አስተዳደራዊ ጉዳዮች የሚኖረው ነጻነት እንደተጠበቀ ሆኖ ተጠሪነቱ ለኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት ስራ አስፈጻሚ ይሆናል፡፡

<u>አንቀጽ-4</u>
<u>የዘካ ኮሚሽን ኃላፊነትና ተግባራት</u>

የዘካ ኮሚሽኑ የሚከተሉት ኃላፊነትና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. በመሰረታዊ የሸሪዓ ህግ መርሆችና በየወቅቱ በሚሰጡ ፈትዋዎች መሰረት ዘካ የማውጣት ግዴታ ካለባቸው ግለሰቦችና ተቋማት የዘካ ገንዘቦችን እና ንብረቶችን ከሀገር ውስጥ እና ከሀገር ውጪ ማሰባሰብ፣
2. ከዘካ የሚገኙ ገንዘቦችን እና ንብረቶችን በመሰረታዊ የሸሪዓ ህግ መርሆችና በየወቅቱ በሚሰጡ ፈትዋዎች መሰረት ዘካ ለሚገባቸው ግለሰቦች፣ ተቋማትና ስራዎች ማከፋፈል፣
3. በሀገራችን የዘካ አሰባሰብና አከፋፈል ስራ ግልጽነት፣ ተጠያቂነትና ተዓማኒነት ባለው መልኩ መከናወኑን የሚያረጋግጥ አሰራር ያለው ተቋም መገንባት፣
4. የዘካ አሰባሰብ፣ አከፋፈልና ጠቅላላ ከዘካ ጋር የተያያዙ ተግባራት አስተዳደር ቀልጣፋና ዘመናዊ በሆነ መልኩ እንዲሰራ የአሰራር ስርዓት መዘርጋት፣
5. በዘካ የሚሰበሰብ ገንዘብና ንብረት በመሰረታዊ የሸሪዓ ህግ መርሆችና በየወቅቱ በሚሰጡ ፈትዋዎች መሰረት ለዘላቂ የድህነት ቅነሳ ስራ ላይ የሚውልበትን ስልታዊ እቅድ በማውጣት ተግባር ላይ ማዋል፣

6. ከወለድ ነፃ የፋይናንስ አግልግሎት ተቋማት በመሰረታዊ የሸሪዓ ህግ መርሆችና በየወቅቱ በሚሰጡ ፈትዋዎችና በሀገራችን ከኢስላሚክ ፋይናንስ ጋር በተያያዘ የወጡ መመሪያና ደንቦች መሰረት ማውጣታቸውን መከተታተል፡፡
7. እነዚህ የፋይናንስ ተቋማት ይህንን ህጋዊ ግዴታቸውን በአጋባቡ እንዲወጡ ከብሔራዊ ባንክና ከሌሎች የሚመለከታቸው የግልና የመንግስት ተቋማት ጋር በትብብር መስራት፤
8. ተቋማቱ የሚሰጧቸውን የዘካ ገንዘቦች በመሰብሰብ የሸሪዓ ህጉ በሚፈቅደው መሰረት ለማህበረሰቡ ጥቅም እንዲውሉ ማድረግ፤
9. የዘካ ጥናት እና ምርምር ማድረግ፣ የምርምር ውጤቶችን ማሳተም፣ ማሰራጨት፣ አውደርዕይ፣ ሴሚናሮች፣ ትምህርታዊ ፕሮግራሞች እና የሌሎች ሀገራት ተሞክሮዎች ማስጠናትና መጠቀም እንዲሁም የዳዕዋ ፕሮግራሞች ማካሄድ፤
10. በዘካ ከሚሰበሰብ ገንዘብ ላይ ሳይቀነስ ከሌሎች በሸሪዓው የተፈቀዱ ምንጮች ፈንድ በማፈላለግ የዘካ ገንዘብ በማህበረሰቡ ህይወት ላይ አዎንታዊ ለውጥ እንዲያመጣ የሚረዱ የልማትና አስተዳደር ተቋማትን መመስረት፣ ማጠናከር፣ ማገዝና ማስተዳደር፤
11. በዘካ ከሚሰበሰብ ገንዘብ ላይ ሳይቀነስ ከሌሎች በሸሪዓው የተፈቀዱ ምንጮች ፈንድ በማፈላለግ በኮሚሽኑ ስም ንብረት ማፍራት፣ መቀበል፣ መግዛት፣ መሸጥና ሌሎች ተግባራትን መፈጸም፤
12. የዘካ ጉዳዮች ላይ የሕግ እና ፖሊሲ ጥናት በማስጠናት ለመንግስት ማቅረብ፣ ሕጎች እንዲወጡ የሕግ ማእቀፎች እንዲሻሻሉ ጥረት ማድረግ፤
13. ዘካ ለሚሰበስቡ ግለሰቦች እና ተቋማት የአቅም ግንባታ ሥራዎች፣ ስልጠናዎች እና እገዛ ማድረግ፤
14. ከሀገር አቀፍ የመንግስት የድህነት ቅነሳ ፕሮጀክቶች ጋር ተመጋጋቢ የሆኑ እቅዶችን በመንደፍ አፈጻጸሙ ላይ የሸሪዓው ዘካ ህግጋቶችን በጠበቀ መልኩ እገዛ ማድረግ፣ የድህነት ቅነሳና ዘላቂ የልማት ስራ ላይ ለተሰማሩ ግለሰቦች እና ተቋማት ድጋፍ ማድረግ፤
15. አላማውን ማሳካት እንዲችል ከኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት፣ ከሸሪዓ ፍርድ ቤት፣ ከወቅፍ ኮሚሽን፣ ከመንግስት ተቋማት፣ ከባንኮች፣ በጎ አድራጎት ድርጅቶች፣ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች፣ ከግለሰቦች፣ ከአለምአቀፍ ተቋማት፣ ከኤምባሲዎች፣ ከሀገራት ተቋማት እና ግለሰቦች እንዲሁም ከሌሎች ጋር በትብብር መስራት፤
16. ከአላማው ጋር ተያያዥ የሆኑ ሌሎች ስራዎችን ማከናወን፡፡

አንቀጽ-5
የኮሚሽኑ አደረጃጀት

1. ኮሚሽኑ 25 አባላት ያሉት የዘካ ኮሚሽን ባለአደራ ቦርድ፣ ተቆጣጣሪ ኮሚቴ፣ የዘካ ኮሚሽን ኮሚሽነርና ሌሎች ለስራው አስፈላጊ የሆኑ ኮሚቴዎችና የአስተዳደር አካላት ይኖሩታል፡፡

THE ETHIOPIAN ISLAMIC AFFAIRS SUPREME COUNCIL

2. የኮሚሽኑ የመጀመሪያ ባአደራ ቦርድ አባላት በኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት ስራ አስፈጻሚ ተመልምለው በጠቅላይ ምክር ቤቱ ፕሬዝዳንት አቅራቢነት በጠቅላይ ምክር ቤቱ ጠቅላላ ጉባዔ የሚሾሙ ይሆናል፡፡
3. በዚሁ መሰረት የጠቅላይ ምክር ቤቱ ፕሬዝዳንት ፊርማና ማህተም ያረፈበት የሹመት ደብዳቤ የተሰጣቸው ግለሰቦች የኮሚሽኑ የመጀመሪያ ባለአደራ ቦርድ አባላት ሆነው ተሰይመዋል፡፡
4. የኮሚሽኑ ስራዎች ከመሰረታዊ ሸሪዓ ህግና ተፈጻሚነት ባላቸው ፈትዋዎች መሰረት መከናወናቸውን የሚከታተል ከኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት ዑለማ ጉባዔ ጋር በመተባበር የሸሪዓ አማካሪ ቦርድ ይኖረዋል፡፡
5. በዚሁ መሰረት የጠቅላይ ምክር ቤቱ ፕሬዝዳንት ፊርማና ማህተም ያረፈበት የሹመት ደብዳቤ የተሰጣቸው 9 ዑለሞች የመጀመሪያ የዘካ ኮሚሽን ሸሪዓ አማካሪ ቦርድ አባላት ሆነው ተሰይመዋል፡፡

አንቀጽ-6
የቦርዱ አደረጃጀትና የስራ ዘመን

1. ኮሚሽኑ ከቦርድ አባላት መካከል በአብላጫ ድምጽ በቦርዱ የመጀመሪያ ስብሰባ የሚሾምና በቦርዱ አባላት 1/3ኛ ድምጽ ጠያቂነት በ2/3ኛ ድምጽ በማንኛውም ወቅት ሊነሳ የሚችል የቦርድ ሰብሳቢ፣ ምክትል ሰብሳቢ፣ ዋና ጸሐፊና ምክትል ጸሐፊ ይኖሩታል፡፡
2. የኮሚሽኑ የቦርድ አባላት የሥራ ዘመን 5(አምስት) አመት ሲሆን አንድ የቦርድ አባል በተከታታይ ከሁለት የስራ ዘመን በላይ ሊመረጥ አይችልም፡፡
3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ለስራ ቀጣነትና ልምድ ልውውጥ ሲባል የስራ ዘመናቸውን ከጨረሱ የቦርድ አባላት መካከል ከ1/3ኛ ያልበለጡት ለሶስተኛ ጊዜ ሊመረጡ ይችላሉ፡፡

አንቀጽ-7
የቦርዱ ስልጣንና ተግባር

የዘካ ኮሚሽን ቦርድ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤

1. ኮሚሽኑን በበላይነት ይመራል፣ ይቆጣጠራል፣ የኮሚሽኑን ኃላፊነትና ተግባራት ተፈጻሚነት ያረጋግጣል፤ ይቆጣጠራል፤
2. በአብላጫ ድምጽ የኮሚሽኑን ኮሚሽነር ቦርዱ በሚያወጣው መስፈርት መሰረት ላልተወሰነ ጊዜ ይቀጥራል፤ ከቦርድ አባላት 1/3ኛ ድምጽ በሚቀርብ ጥያቄም በ2/3ኛ ድምጽ ያሰናብታል፤
3. የኮሚሽኑን አደረጃጀትና የአሰራር ስነስርዓት መመሪያዎች ያወጣል፤
4. የራሱን የስብሰባ አካሄድና አሰራር ስነስርዓት መመሪያ ያወጣል፣

5. የኮሚሽኑን የግዢና ፋይናንስና አስተዳደር ማኑዋል እንዲሁም የአመራሮችና ሌሎች ሰራተኞች የቅጥር መስፈርትና ስራ መዘርዝር ያወጣል፣
6. የኮሚሽኑን ቦርድ አባላትና የሸሪዓ ተስማሚነት አማካሪ ኮሚቴ አባላትን አበል ለጠቅላይ ምክር ቤቱ በማቅረብ ያስጸድቃል።
7. የቦርዱ ስራ ዘመን ሊጠናቀቅ 6 ወራት ሲቀረው የቀጣይ ስራ ዘመን ቦርድ አባላትን የሚመለምል ገለልተኛ ኮሚቴ በማቋቋም እጩዎችን ለጠቅላይ ምክር ቤቱ ፕሬዝዳንት ጽ/ቤት ያሳውቃል።
8. የኮሚሽኑን ዓመታዊ የስራ እቅድና በጀት እንዲሁም የረዥም ጊዜ ስትራቴጂክ (ስልታዊ) እቅድ እንዲዘጋጅ በማድረግ ያጸድቃል ተግባር ላይ መዋሉንም ይቆጣጠራል፤
9. ለኮሚሽኑ ስራ አስፈላጊ የሆኑ ንዑስ ኮሚቴዎችን ያደራጃል፣ የክልል ጽሕፈት ቤቶችን እና ቢሮዎችን ያደራጃል፤
10. የኮሚሽኑን የከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎችን ደሞዝና አስተዳደራዊ ወጪ በጀት ይወስናል፤
11. የቦርዱን ስራዎች በከፊልም ሆነ ሙሉ በሙሉ ከአባላቱ ውስጥ ለሚሰየም ንዑስ ኮሚቴ በውክልና ይሰጣል።
12. ኮሚሽኑ ከሌሎች እስላማዊ የሀይማኖት አስተዳደር ተቋማት ጋር ለተወሰነም ሆነ ላልተወሰነ ጊዜ በጋራ የሚሰራበትን ስምምነት ያደርጋል።
13. ሌሎች የኮሚሽኑን ዓላማዎች ለማሳካት የሚያስፈልጉ ተግባራትን ይፈጽማል፤ ያስፈጽማል፤

አንቀጽ-8
የኮሚሽነሩ ስልጣንና ተግባር

1. ኮሚሽነሩ ተጠሪነቱ ለቦርዱ ወይም ቦርዱ ለወከለው ኮሚቴ ሆኖ የኮሚሽኑን የእለት ተእለት ስራ ይመራል ያስተባብራል፤
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ስር የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ኮሚሽነሩ፡-
   ሀ. የዘካ አሰባሰብ ዘርፍና ዘካ አከፋፈል ዘርፍ ምክትል ኮሚሽነሮችን በመመልመል በቦርዱ እንዲሾምለት ያቀርባል፤
   ለ. ይህንን ደንብና ቦርዱ የሚያወጣቸውን መመሪያና ማኑዋሎች ተፈጻሚ ያደርጋል፤
   ሐ. ቦርዱ በሚያጸድቀው የቅጥርና የሰራተኛ አስተዳደር ማኑዋል መሰረት የኮሚሽኑን ሰራተኞች ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣ ያሰናብታል፤
   መ. የኮሚሽኑን ዓመታዊ የስራ እቅድና ረቂቅ በጀት በማዘጋጀት ለቦርዱ ያቀርባል፤ ሲፈቀድለትም ስራ ላይ ያውላል።
   ሠ. በቦርዱ በተፈቀደለት የአስተዳደራዊ ወጪዎች በጀት መሰረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል።
   ረ. ኮሚሽኑን በመወከል በሰነዶች ላይ ይፈርማል፣ ውሎች ይዋዋላል፤
   ሰ. ሌሎች በቦርዱ የሚሰጡትና ስልጣንና ተግባራት ያከናውናል።

አንቀጽ-9

ዓርማ፣ማህተም፣ቢሮ፤ሰራተኞች

8.1. ኮሚሽኑ በቀላሉ የሚለይበትን እና አላማውን ገላጭ የሆነ አርማ ይኖረዋል፤

8.2. ኮሚሽኑ የሚገለገልበት ማህተም ይኖረዋል፤

8.3. ኮሚሽኑ ሥራዎቹን የሚሰራበት የራሱ ዋና መ/ቤትና እንደ አስፈላጊነቱ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በሀገራችን የተለያዩ ክልሎችና በውጪ ሀገር ይኖረዋል፤

8.4. ኮሚሽኑ ለስራው የሚያስፈልጉ ቋሚና ጊዜያዊ ሰራተኞችንም ይቀጥራል፤

አንቀጽ-10

የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ ደንብ በሁሉም ደረጃ ባሉ የኢትዮጲያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት፣ በክልል እስልምና ጉዳዮች ምክር ቤቶች፤ እስከ ወረዳ ድረስ ባሉ የመጅሊስ ምክር ቤቶች፣ በመስጂዶች በሃላል ተቋማት እና በኢትዮጵያውን ሙስሊሞች በትውልደ ኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች ላይ ተፈፃሚ ነው።

አንቀጽ 11

የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

1. ኮሚሽኑ ይህ ደንብ ከመውጣቱ በፊት የነበሩ የዘካ ሰብሳቢ አካላትና የዘካ አሰባሰብ ስርዓቶችን ይመዘግባል፣ እውቅና ይሰጣል፣ የአስተዳር መመሪያ ያዘጋጃል፣ ስልጠና ይሰጣል፣
2. ከነባር ተቋማቱ ጋር በትብብር ይሰራል፣ እንደ አስፈላጊነቱም ስራውን በህጋዊ መንገድ ተረክቦ ሊሰራ እና ሊያስተዳድር ይችላል።

አንቀጽ 12

የማሻሻያ ድንጋጌዎች

ይህ ደንብ ከኮሚሽኑ ባለአደራ ቦርድ አባላት በ1/3ኛው ጥያቄ በሚቀርብበት ጊዜ በ2/3ኛ ድምጽ በከፊል አለያም ሙሉ ለሙሉ ሊሻሻል ይችላል።

አንቀጽ 13

ደንቡ ስለሚጸናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በቦርዱ ከጸደቀበት እለት አንስቶ የጸና ይሆናል።

ጥቅምት 2018/ጁማዱል ኡላ 1447

ሼህ ሀጅ ኢብራሂም ቱፋ

የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት ፕሬዚደንት

የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ም/ቤት

Ethiopian Islamic Affairs Supreme Council

المجلس الأعلى للشؤون الإسلامية في إثيوبيا

ልዩ ቁጥር m/ም/287/26/46/18

ቀን 18/10/2018

ማቋቋሚያ ምስክር ወረቀት

በኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ም/ቤት «የኢትዮጵያ ዘካት ኮሚሽን» የራሱ ህጋዊ ሰውነት ያለው የህግ ሰው ሆኖ በህገ መጅሊሱ አንቀጽ 80 (1) እና በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ህዝብ ተወካዮች ም/ቤት አዋጅ ቁጥር 1207/2012 አንቀጽ 2(1) መሠረት የተቋቋመ መሆኑን ለማረጋገጥ ይህ የምስክር ወረቀት ተሰጥቶታል።

Certificate of Establishment

This Certificate of establishment has been given to The Ethiopian Islamic Affairs Supreme Council "**Ethiopian Zekat Commission**" to grant a legal personality as per article 80(1) of the Mejils Regulation & article 2(1) of the FDRE House of people's representatives proclamation No. 1207/2020

شهادة التأسيس

تمنح هذه الشهادة لهيئة الزكاة الإثيوبية التابعة للمجلس الأعلى للشؤون الإسلامية في إثيوبيا، لمنحها الشخصية القا نونية، وفقاً للمادة 80 (1) من لا ئحة المجلس والمادة 2 (1) من إعلان مجلس نواب الشعب لجمهورية إثيوبيا الفدرالية الديمقراطية تحت رقم الإعلان الدستوري 1207/2012

የክብር ዶ/ር ሸይኽ ሐጂ ኢብራሂም ቱፋ
የኢ/እ/ጉ/ጠ/ም/ቤት እና የዑለሞች ጉባኤ ፕሬዝዳንት

H.E. Dr. Sheikh Haji Ibrahim Tufa
President of E.I.A.S.C & Ulema Assembly

معالى د/ الشيخ حجي إبراهيم توفا
رئيس المجلس الأعلى للشؤون الإسلامية ورئيس هيئة العلماء في إثيوبيا

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የገቢዎች ሚኒስቴር
Federal Democratic Republic of Ethiopia
MINISTRY OF REVENUES

የግብር ከፋይ ምዝገባ ሰርተፊኬት
TAXPAYER REGISTRATION CERTIFICATE

የግብ ከፋይ መለያ ቁጥር: Taxpayer Identification Number:	0108579717
የድርጅት/የግለሰብ ሥም: Name of Business/Individual:	የኢትዮጲያ አውቃፍ ኮሚሽን ETHIOPIAN AWEQF COMMISSION
የተመዘገበ አድራሻ/Registered Address:	
ክልል: Region:	አዲስ አበባ ADDIS ABABA
ዞን/ክ.ከተማ: Zone/Sub City:	ከልፌ ቀራንዮ KOLFIE KERANIYO
ወረዳ: Woreda:	
ቀበሌ /በአማርኛ/: Kebele/Farmer's Assoc.:	ወረዳ 10 WOREDA 10
የቤት ቁጥር: House No.:	002
ESIC Sub-group: ESIC Sub-group:	92131 - Medical and social welfare support services
የሰጠው ተቋም: Issuing Authority:	የገቢዎች ሚኒስቴር MINISTRY OF REVENUES
የተሰጠበት ቀን: Date of Issuance:	24 SENE 2018 01-JUL-26

ይህ የምስክር ወረቀት የግብር ከፋዩን ብቸኛ የግብር ከፋይነት ምዝገባ ሲሆን ከዚህ ቀደም የነበሩ የግብር ከፋይነት ምዝገባ ሰነዶች ካሉ በዚህ ሰነድ የተተኩ መሆናቸውን ነው።
ከላይ በተጠቀሰው መረጃ ላይ ማንኛውም አይነት ለውጥ ቢደረግ ግብር ከፋዩ ለሚመለከተው የግብር ሰብሳቢ ጽ/ቤት የማሳወቅ ግዴታ አለበት።

This certificate represents the sole and only registration as a taxpayer and supersedes all prior registration documentation.
The taxpayer is responsible for notifying the appropriate Tax Office of any changes to the above information.

የሰርተፊኬት ቁ.:
Certificate No.: 2096860331696

ህሊና ሳህሌ ተክሌ
የታክስ ከፋዮች ክፍተት
የምዝገባ ...

የባለሥልጣኑ መ/ቤት ማህተም
Seal of Issuing Authority

B.S.S.P.E